# የእምቧይ ካብ ስብስቦቹ አስገራሚ “ሰነድ”

**መስፍን አለሙ**

12-6-14

እርግጥ ነው— “ዘጠኝ ነን” ብለዋል። በአንድ ጎሬ ውስጥም መሰባሰባቸውንም ነግረውናል። አንዳንዶቹን ከዚህ ቀደም ውልደታቸውን እንኳን ሰምቼላቸው አላውቅም። ብቻ ተቧድነዋል። “ሰማያዊ” የተሰኘውንና ሃይማኖትና ፖለቲካ የተምታቱበትን ፓርቲ የሚመሩት “ባለ ቀለሙ” ሰውዬ ኢንጂነር ይልቃል ጌትነት ከየት ለቃቅመው ጎሬያቸው ውስጥ እንዳጎሯቸው እንኳንስ እኔ እርሳቸውም የሰከነ አዕምሮ ካላቸው ረጋ ብለው ቢያስቡት (ማሰብ ከቻሉ ማለቴ ነው) እንኳን ዕውነታው የሚከሰትላቸው አይመስለኝም።

ለነገሩ ሰውዬው ሰብስበው ስለያዟቸው ጥቃቅንና አነስተኛ የተቃውሞ ጎራ ባለሚሎች ማንነት ደንታ የላቸውም—እሳትና ጭድ ሆነው በጠላትነት የሚፈላለጉ ቢሆኑም እንኳን ጉዳያቸው አይደለም።...ርሳቸው ምን ተዳቸው ጃል!?....የሚፈልጉት በባዶ ሜዳ ላይ ብዙ ሆኖ በመታየት ለአለቆቻቸው አክራሪ ኒዮ-ሊበራል ሃይሎች መስሎ መገኘትን ብቻ ነው— በሌለ ማንነት አውላላ ሜዳ ላይ ተቆልሎ የመታየት አጉል አባዜ። ከፅንፈኞች በሚገኝ ዳረጎት የኪራይ መሰብሰቢያ አኮፋዳቸውን መሙያ ትርዒት።

ታዲያ በሰውዬው ተጣምረው አሊያም እንዲጣመሩ ትዕዛዝ ተሰጥቷቸው “ለመተባበር አንድ ሆነናል” ያሉት ዘጠኙ ፓርቲዎች፤ ያው እንደተመደው የሀገሪቱ ችግር “ሁሉን አወቆችና ተንታኞች፣ ከፍ ሲልም አዚህና እዚያ የሚረግጥ ሰነድ አውጭዎች” ሆነው ቀርበዋል። በእኔ እምነት ምንም እንኳን እነዚህ ፓርቲዎች ህገ-መንግስቱ ባጎናፀፋቸው መብት ተጠቅመው መደራጀታቸው አግባብ ቢሆንም፤ በተቧደኑ በሳምንቱ አፋቸውን የሚያሟሹት ከጋራ አጀንዳቸው ይልቅ በችግሮች ለፋፊነታቸው መሆኑ እጅግ የሚያስገርም ነው።

እንደ እውነቱ ከሆነ ሁሉም የተቃውሞ ጎራ ከትናንት የማይማሩ እንዲሁም ለነገ አንዳችም ራዕይ የሌላቸው መሆናቸው የወል ባህሪያቸው ነው ማለት ይቻላል። እንደ እንቧይ ካብ

ይሰባሰቡና ለመበታተን ጊዜ የማይወስድባቸው አስቂኞች መሆናቸው የትናንት ማንነታቸው፣ የዛሬም ገቢራዊ ድርጊታቸው አፍ አውጥቶ ይናገራልና።

ታዲያ በዛሬው ፅሑፌ ለቀለም አብዮት ማሰፍሰፋቸውን በአንድ ወቅት የፓርቲያቸው ልሳን በሆነው "ነገረ-ኢትዮጵያ" በተሰኘ ነገር አቀጣጣይ ጋዜጣ ላይ የለፈፉት ኢንጂነር ይልቃል የሚመሩት የዘጠኙን የእምቧይ ካብ ስብስቦች "ሰነድ" ተብዬ ሰሞነኛ ድርሳንን በደምሳሳው ለመቃኘት እሞክራለሁ።

በቅድሚያ ግን የሀገራችንን ተቃዋሚዎችን አሳፋሪ የጋራ ባህሪያት ብንመለከት ጠቃሚ ይመስለኛል። ለምን? ቢሉ፤ የተቃውሞው ጎራ እንኳንስ ሀገር ሊመራ ቀርቶ፤ ራሱንም በቅጡ ማስተዳደር የማይችል የእንቧይ ካብ ስብስብ መሆኑን ከትናንትም ይሁን ከዛሬ ዳራው በሚገባ እንድናውቀው ስለሚያደርገን ነው።…

…ሁሉም ሊባሉ በሚችል ሁኔታ የሀገራችን ተቃዋሚዎች ይህ ነው የሚባል በግልፅ የሚታወቅና ህዝብን በዙሪያቸው ሊያደራጁ የሚችሉበት አማራጭ የላቸውም፡፡ ተቃዋሚዎቹ ላይ ላዩን ሲያዩዋቸው የሊበራሊዝም አቀንቃኝ ይመስላሉ፡፡ ይሁንና እውተኛ ማንነታቸው ሲፈተሽ፤ እነዚህ ኃይሎች የሚመሩት ከዚህም ከዚያም በተቃረሙና "በተቦጫጨቁ" ሃሳቦች መሆኑን መገንዘብ አያዳግትም፡፡

እነዚህ የተቀነጫጨቡ ሃሳቦችም ወጥ ያልሆኑና ያልተዘረዘሩ ናቸው፡፡ ላይስሙላ ካልሆነ በስተቀር ሰላማዊ የፖለቲካ ትግል የሚባል ነገርንም አያውቁትም፡፡ እንደ ተቃዋሚ ፓርቲ በተከታታይ ትምህርትና ውይይት ህዝብን ማሳመን የሚባል ነገርም በእነርሱ ዘንድ እንደ ጸያፍ ተግባር የሚታይ ነው፡፡

ለእነዚህ ወገኖች ከልምድ መማር ማለት "አድሮ ቃሪያ" እንደመሆን የሚቆጠር ነው፡፡ እናም ትናንት በነበሩበት ቦታ ላይ፤ ዛሬም አሮጌ ድርሳናትን አዋራቸውን ሳያራግፉ መግለጥን እንደ ትክክለኛ የፖለቲካ ስልት የሚከተሉ አስገራሚ ስብስቦች ናቸው፡፡ በምርጫ 97 ወቅት ያስነሱት የጎዳና ላይ ነውጥ ዛሬም ድረስ የሚሰራ ይመስላቸዋል፡፡

አክራሪው የተቃውሞ ጎራ በዚህ ባህሪያዊ ማንነቱ፤ በተለይም ከህገ - መንግስታዊ ስርዓቱ ጋር በፈጠረው እሰጥ አገባ በምርጫ 2002 በህዝቡ ካርድ አሳፋሪ ሽንፈትን

ሊከናነብ ችሏል፡፡ ታዲያ ጎራው በራሱ ፀረ - ህገ - መንግስታዊ ተግባራት ከመጸጸት ይልቅ፣ በህዝቡ ላይ ቂም መያዝን ነው የመረጠው። ይህም "ቂም -አንድ" ተብሎ በቅርብ ጊዜ ትውስታነት ሊፈረጅ ይችላል፡፡

በሰሜን አፍሪካ የተነሳውን ህዝባዊ አመጽ ተከትሎ፣ 'አመጹ ኢትዮጵያ ውስጥ መነሳት ይኖርበታል' በሚል እምነት በመያዝ የሀገራችንን ህዝብ ለዚህ ተግባር የተቋቋሙ በሚመስሉ አንዳንድ የግል ጋዜጦች አማካኝነት "አትነሳም ወይ..." እያለ ቢቀሰቅስም፣ የአመጽ ጡሩንባው ጭው ባለ በረሃ ላይ የተነፋ ይመስል ፍላጎቱ በህዝቡ በሳልና ሚዛናዊ እሳቤ ሳቢያ መክኖ ቀርቷል፡፡ የዚህ ጽሑፍ አንባቢ፣ ምናልባትም በዚህ የህዝቡ "ጆሮ ዳባ ልበስ " ምላሽ የበገነውን የአክራሪውን ቁጭት "ቂም-ሁለት" ብሎ ሊመዘግበው ይችላል፡፡

የፀረ -ሠላምና የማጭበርበር ስልቶችን የሚከተለው የተቃውሞው ጎራ፣በዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅዱ እንዲሁም በታላቁ የህዳሴ ግድብ ግንባታ ላይ የማደናገሪያ ሃሳብ ይዞ ብቅ ከማለት አልቦዘነም፡፡ የአክራሪውን "ቡድን" እንመራዋለን የሚሉ ግለሰቦች ከእንቅልፋቸው በባነኑ ቁጥር ድንገት እየተነሱ 'ዕቅዱ የማይሳካ ነው፣ ለፖለቲካ ፍጆታ ሲባል በመንግስት የተያዘ ትልም ነው' በሚል ህዝቡን ከልማት ርብርቡ ሊያዘናጉት ያልሞከሩበት ጊዜ አልነበረም፡፡

ህዝቡ ግን "ዕቅዱ የነገ ማንነቴን የምገልጽበት እንዲሁም ከተመጽዋችነት የምላቀቅበት ስለሆነ ወግዱ እናንተ አደናቃፊዎች" የሚል ምላሽ በመስጠቱ፣ ፀረ -ልማት የሆኑት ወገኖች እጢያቸው ዱብ ብሏል፡፡ ይህም የቡድኑን "መለያ" በለበሱት ኃይሎች ዘንድ እንደ " ቂም - ሦስት" የተቆጠረ ነው ማለት ይቻላል፡፡

በታላቁ የኢትዮጵያ ህዳሴ ግድብ ዙሪያም፣ ይህ ፀረ-ሀገራዊ ልማት "ቡድን" የግድቡን ግንባታ በመጻረር ያልደሶከረው የወሬ ዓይነት እንደሌለ እናስታውሳለን፡፡ የህዝቡን ከጫፍ ጫፍ የመነሳሳት ወኔን ለመስለብም "ግድቡ የህዝቡን አመጽ ለማስቀየር የቀረበ ነው" ከሚለው የ"ላም አለኝ በሰማይ..." ህልሙ ጀምሮ፣ ለአንዳንድ የሙባረክ ዘመን ቅሪት የግብጽ ጋዜጦች ወሬ እስከ ማቀበል ድረስ የደረሰ ፀረ- ኢትዮጵያ አቋሙን አራምዷል– 'ምናልባት አዲሱ የካይሮ መንግስት ይደግፈኝ ይሆናል' የሚል ዘግናኝ የባንዳነት የተስፋ ዳቦን ሰንቆ፡፡

ይሁንና የተቃውሞ ጎራው ያሻውን ቢለፍፍም፤ ህዝቡ ግን ከመጤፍ አልቆጠረውም፡፡ የህዳሴው ግድብ ግንባታ እውን እንደሚያደርገው ስለተማመነ፤ የአደናቃፊዎቹን ፀረ - ልማት የከበሮ ድለቃ ሊሰማ አልፈለገም፡፡ እንዲያውም ለግንባታው በገንዘቡ፣ በጉልበቱና በእውቀቱ ከሚያበረክተው አስተዋጽኦ ባሻገር፤ የቦንድ ግዥውን በማጧጧፍ ልክ ግብጽ ውስጥ እንዳሉት ጥቂት "የሙባረክ መንፈስ" አራማጆች ሁሉ፤ የሀገራችንን አክራሪ ተቃዋሚንም ወሽመጡን ቆርጦታል፡፡ ይህም "በቂም -አራትነት" በአክራሪው ቡድን የተያዘ ነው ማለት ይቻላል፡፡

በዚህ ጽሑፍ አቅራቢ እምነት፤ ህዝቡ የተቃውሞውን ጎራ ፀረ - ሠላም የአመጽ ጥሪንና ፀረ - ልማት ዲስኩሩን ያልሰማው በሁለት ምክንያቶች ነው፡፡ አንደኛው ማንኛውንም ጊዜያዊ ችግሮች መፍታት የሚችል ልማታዊና ዴሞክራሲያዊ መንግስት ያለው መሆኑን በመገንዘቡ ሲሆን፤ ሁለተኛው ደግሞ የህዝቡ ንቃተ ህሊና ከተቃዋሚ ተብዬው ኃይል የትየለሌ ልቆ በመገኘቱ ነው፡፡

ታዲያ እውነታው ይህ ሆኖ ሳለ፤ ተቃዋሚው ቡድን ቀደም ሲል በጠቀስኳቸውና በሌሎች "ቂሞቹ" በመታገዝ 'ህዝቡ ለምን ያልኩትን አይሰማም?' ከሚል አንባገነናዊና ፀረ - ህዝብ ባህሪው ተነስቶ ፣ ለሰላምና ለልማት የዘመተውን ህዝብ መሳደብ፣ መናቅና ማንቋሸሽ ከጀመረ ብዙ ጊዜ ሆኖታል፡፡

በየትኛውም ሀገር ሊፈጠሩ የሚችሉ ችግሮችንና ነባራዊ እውነቶችን በማጋነንና ብሶትን በማራገብ አመጽ ለመቀስቀስ ብሎም ፀረ - ልማት ተግባር ለመከወን አስቦ፤ በህዝቡ ሚዛናዊ፣ ፍትሐዊና አስተዋይ ማንነት ሳቢያ የጨነገፈበት ጎራው፣ ወደ ንቀትና ማንቋሸሽ መናኸሪያነት ተለውጧል፡፡ ባረገዛቸው "ቂሞች" እየተገፋፉም "ፈሪ ሆኗል፣ ሀሞቱ ፈሷል፣ ወኔው ተሰልቧል...ወዘተ." በሚሉ ፀያፍ ንግግሮች፤ ይህን ሰላም፣ ልማትና ዴሞክራሲ ወዳድ ህዝብን በይፋ እየዘለፈውና እያንቋሸሸው እንደነበርም የቅርብ ጊዜ ትውስታችን ነው፡፡

ምንም እንኳን በአንድ ዴሞክራሲያዊ ሀገር ውስጥ ሉዓላዊ የስልጣን ባለቤት የሆነው ህዝብ በሚይዘው አቋም የማይዘለፍና የማይንቋሸሽ ቢሆንም ቅሉ፤ የተቃውሞው ጎራ ግን ይህን የህዝቡን መብት ያልተጋፋበትን ጊዜ አላስታውስም። በአንድ ወቅት እንኳን "መድረክ"

የተሰኘው የእሳትና ጭድ ስብስብ መንግስት በፈጠረለት ምቹ ሁኔታ በስራ ባተሌ የሆነውንና የህብረተሰቡ አንድ አካል የሆነውን ወጣት በይፋ "ብልጭልጭ ነገር ያታልለዋል" በማለት ያለ ስሙ ስም እንደሰጠው አስታውሳለሁ።

ነገሩ "ስም ያጣ መድረክ ወደ የተባለው እርስ በርሱ የሚቦጫጨቅ ፓርቲ ይምጣ" የተባለ ይመስል፤ "መድረክ" አጠቃላይ ህዝቡን ከማንቋሸሽ ባለፈ ለሀገሩ ምጣኔ ሃብታዊ ዕድገት ሌት ተቀን በመስራት ላይ ያለውን ወጣት እንዲህ መዝለፉ የተቃውሞው ጎራ ቅጥ የለሽነት እስከ የት ድረስ እንደሚደርስ ሁነኛ አስረጅ ይመስለኛል።

የተቃውሞው ጎራ አሳፋሪ የወል ባህሪ ማንነት በዚህ ብቻ የተገታ አይደለም። የጎራው መሰባሰቢያ በማንኛውም ጊዜ ሊፈርስ የሚችል "የድንቡሽት ቤት" ነው፡፡ ጣሪያና ግድግዳውን ደግፈው የያዙት "ውጋግራዎች" በአግባቡ የተዋደዱ አይደሉም፡፡ አንደኛው "ውጋግራ" ሌላኛውን ስለማያውቀው ለየት ያለ ነባራዊ ክስተት በተፈጠረ ቁጥር፤ ቤቱ እንደ ውኃ ላይ ኩበት ከመቅጽበት ይንሳፈፋል፡፡ "ምሰሶው" የተገነባው ብዙም ጊዜ ከማይቆየውና "ጭፍን ጥላቻ" ከሚባለው እርባና የሌለው የእንጨት ዓይነት በመሆኑም፤ የቤቱ አባላት በሆኑት "ተቃዋሚ ብሎች" በቀላሉ ተቦርቡሮ በማንኛውም ጊዜ ሊወድቅ የሚችል ነው፡፡

ይህ አባባል የተቃውሞውን ጎራ ማንነት ቁልጭ አድርጎ የሚያሳይ ተምሳሌታዊ ዕውነታ ነው፡፡ "ቤቱ" እንደ "መድረክ" ዓይነት የጎራውን መሰባሰቢያ ስያሜን ሲያመለክት፤ "ውጋግራው" እና "ብሎቹ" ደግሞ እርስ በርሳቸው የማይተማመኑትንና አንደኛው ሌላኛውን በጎሪጥ የሚያዩትን "የእምቧይ ካብ" የተቃዋሚ ፓርቲዎችን ይወክላሉ፡፡

የፓርቲዎቹ የጥምረት ምስጢርም በ"ምሰሶው" ተመስሏል–በጭፍን ጥላቻ፡፡ ታዲያ በዚህ ዕድሜ በሌለው "ምሶሶ" "በየትም ፍጪው ዱቄቱን አምጪው" ብሂል የተጣመሩት "የኛዎቹ" ጉደኞች መበተናቸውን ለመናገር ያላቸው ፍጥነት ትናንት አብረው የነበሩ እንኳን አይመስሉም፡፡ እዚህ ላይ ሰሞነኛውን የአንድነትንና የመድረክን ይፋዊ "ፍቺ" ያስታውሷል!

አንደኛው "ውጋግራ" ከሌሎቹ ጋር የተማማለበትን "የጭፍን ጥላቻ" መርህ ተመርኩዞ፤ በመንግስት ላይ የመግለጫ  ጋጋታ ያወጣል፡፡ ሌላኛውም 'እኔስ እንዴት እበለጣለሁ' በሚል ቁጭት የራሱን 'ነጠላ ዜማ' ይለቃል፡፡

‘ነጠላ ዜማው’ ግጥሙ ቤት ይምታ፣ አይምታ ለእርሱ ደንታው አይደለም፡፡ የዜማው ስልተ - ምት ከነባራዊው ሀገራዊ ሁኔታ ጋር ቢጣጣም ፣ ባይጣጣም እርሱ ምን ገዶት? - ብቻ መንግስት ማጥላላት እስከቻለ ድረስ የጥላቻ አታሞውን ይዞ ይደልቃል፤ ይውረገረጋል፤ ያቅራራል፡፡...

የእርሱን መውረግረግ ተከትለውም፤ “የውጋግራው” ማስተንፈሻ አሊያም መወሽቂያ ሆነው የሚያገለግሉት አንዳንድ የግል መገናኛ ብዙሃን ‘በርታ ጀግናዬ! ምን ነበር ያልከው?’ በማለት ጉዳዩን የጋዜጣ ማሻሻጫ ያደርጉታል - እግረ መንገዳቸውንም የራሳቸውን ስውር ዓላማ እያሳኩ፡፡ እርግጥ “የውጋግራው” ጭፍን ጥላቻ ጎልቶ የሚወጣው አንድ አክራሪ ኒዮ - ሊበራል ተቋም፤ የራሱን ወይም የሌሎችን ጥቅም ለማስጠበቅ ሲል የሸፋን “ሪፖርት” በሚያወጣበት ሰሞን ነው፡፡ ታዲያ ያኔ ‘ እርሱን አያድርገኝ’ ያስብላል፡፡...

ምናልባት ‘አለቃ ሁሌም ትክክል ነው’ የሚለው ይትብሃልን ገቢራዊ እያደረገ ይሁን ወይም ሌላ፤ “ውጋግራው” የጽንፈኛው ኒዮ - ሊበራሉን የውጭ አሉታዊ “ሪፖርት” ሲሰማ አንዳች ማነቃቂያ ዕፅ የወሰደ ያህል ምላሱ ይፍታታል፡፡ “ሪፖርቱ” ትክክል ይሁን፣ አይሁን የሚያገባው እርሱ ምን ተዳው?... “የሪፖርቱ” ባለቤት የደረሰበት ድምዳሜ፤አግባብ ያለውን ሳይንሳዊ አካሄድን የተከተለ ፣ ሃቅ ላይ የተመረኮዘና ምን ዓይነት ድብቅ ዓላማን ለማሳካት እንደቀረበ እንኳን አያጣራም፡፡

በጭፍን የፖለቲካ ስሜት የሚነዳ በመሆኑም፤ ይባስ ብሎ ሪፖርቱ ያላለውን በመጨማመርና ቆርጦ በመቀጠል የሀገር ውስጥ “ተንታኝ” ሆኖ ያሻውን ይዘላብዳል፡፡...አይ ተቃውሞ!...አይ ህዝብ ወካይ!...አይ አጀንዳ!...አይ ሀገር መሪ!...አይ ተወዳዳሪ!...መቼም ድርጊታቸውን በእነርሱ ቦታ ሆኖ ማየት አንገት ያስደፋል፤ያሳፍራል። ከንቱነታቸውም ገዝፎ ይወጣል። እንደ አለመታደል ሆኖ ሀገራችን እንዲህ ዓይነቶቹን አሳፋሪዎችና ለአቅመ-ተቃዋሚነት ያልደረሱ ተቃዋሚዎችን ሰብስባ መያዟ ያሳዝናል።

እስቲ ይህን የተቃውሞው ጎራን የወል ባህሪ እዚህ ላይ ገታ ላድርገውና ህግና ስርዓትን በመናቅ በማን አለብኝነት እንዳሻው ለመፈንጨት በሚከጅለው የቀለም አብዮት አቀንቃኙ ሰማያዊ ፓርቲ መራሹ የእንቧይ ካብ ስብስቦች “ሰነድን” ወደ መቃኘቱ ልመለስ።...

የእነ ኢንጂነር ይልቃል ጌትነት ስብስብ ተግባሩን የጀመረው ህግና ስርዓትን በመናቅ ነው። ለዚህም ሰነዱን ባቀረበበት ወቅት “ለመተባበር የምርጫ ቦርድን ይሁንታም ሆነ ዕውቅና ማግኘት የለብንም” በማለት አጉራ ዘለልነቱን ለማሳየት ሞክሯል። እርግጥም ምርጫ ቦርድ ፓርቲዎች በሚያደርጓቸው ተግባራትን ማወቅ ይኖርበታል። ይህም እኔ እስሚገባኝ ድረስ ስብስቡ ምናልባት በሚያከናውናቸው ተግባራት የህግ ከለላና ድጋፍ የሚያስፈልገው ከሆነ ምርጫ ቦርድ በቅርበት እየተከታተለ እንዲያግዘው ያደርጋል። አሊያ ግን በህግ የተቋቋመን አካል (ለዚያውም በህጋዊ መንገድ የተቋቋሙ የፖለቲካ ፓርቲዎች ከምርጫ አኳያ ምን እያናወኑ እንደሆነ የመከታተል ኃላፊነትና ግዴታ ያለበትን ምርጫ ቦርድን) ‘እኛ እንዳሻን ብንሆን እርሱ ምን ያገባዋል!’ ማለት ጤነኝነት አይመስልም።

እንዲያውም አባባሉ ራስን ከህግና ስርዓት ጋር ለማጋጨት አስቀድሞ የመዘጋጀት ያህል የሚቆጠር ነው። በመሆኑም የቀለም አብዮት መራሹ ስብስብ የሚመራው በዘፈቀደ ነው ለማለት ይቻላል።

ዳሩ ግን ሁሉም ጉዳዮች ህግን ተመርኩዘው በሚከናወኑበት ዴሞክራሲያዊ ሀገር ውስጥ የፖለቲካ ፓርቲዎች ያለ ከልካይ እንዳሻቸው ሊፈነጩ የሚችሉበት ምህዳር የሌለ መሆኑን ማወቅ ተገቢ ይመስለኛል። እናም በሰበብ አስባቡ ህግና ስርዓትን ከሚያስከብሩ አካላት ጋር ለመላተም የሁከት መደላድል ለመፍጠር መሞከር ተቀባይነት የሌለው ጉዳይ መሆኑን መገንዘብ የሚገባ ይመስለኛል።

መቼም የተቃውሞው ጎራ ‘በእኔ እበልጥ’ ባይነት አንዱን ሌላኛውን ማብጠልጠል መለያ ባህሪው በመሆኑ ይህ “ሰነድም” ከራሱ አልፎም ስለ ሌሎች የተቃውሞ ጎራ ባለሚሎች መዳሰሱን ይናገራል። ምንም እንኳ የሀገራችን ተቃዋሚዎች “ከዝንጀሮ ቆንጆ ማንን ይመርጡ” እንደሚባለው ዓይነት ቢሆኑም፤ ይህ ባለ 13 ገፅ የስብስቡ ሰነድ “የተቃዋሚ ፖለቲካ ጐራ የጋራ ትግል ውጤታማነት ላይ የተደረገ ግምገማና ዳሰሳ” በሚል የቀረበ ነው። ምንም እንኳን ለእኔም ሆነ ለአንባቢዎቼ ዳሳሽና ተዳሳሹ ማን እንደሆነ ግልፅ ባይሆንም፤ “…ወደ ትብብር ከመሄድ በፊት ኢትዮጵያንና ኢትዮጵያዊነትን አስመልክቶ ከፖለቲካዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ማኀበራዊ ጉዳዮች አንፃር በቂ ትንተናና ውይይት ሳያደርጉ በተቻኮለ መንገድ ወደ የጋራ ሥራ መግባት አያስፈልግም” ይላል።

ይሁንና የኢንጂነሩ ፓርቲ ከተመሰረተ ከሁለት ዓመት እንኳን ያልበለጠ ከመሆኑም በላይ እንዴት ተጣድፎ ለመታየት ሲባል ብቻ ከስምንቱ ፓርቲዎች ጋር ራሱን እንዳቆራኘ የሚታወቅ ጉዳይ ነው። እኔ እስሚገባኝ ድረስ እንኳንስ ትብብሩ ቀርቶ የተናጠል ፓርቲዎቹም ቢሆኑ ስለ ተባለው ጉዳይ በቅጡ ሳያውቁ ለመጣመር ብቻ ሲሉ ተጣድፈው ለመተባበር የተሰለፉ ናቸው።

የቀለም አብዮት አራማጁን ሰማያዊ ፓርቲን በአጃቢነት ለመደገፍ የቆሙም ናቸው ማለት ይቻላል። ሚናቸውን እንኳን በቅጡ ለይተው የሚያውቁ አይደሉም። እንዲያውም ተግባራቸው የሁከት ባለሟሉ ሰማያዊ ፓርቲ ደብዳቤ አድራሽ ሆነው ሲንቀሳቀሱ ከሰሞኑ ከአዲስ አበባ መስተዳድር ጋር በሰላማዊ ሰልፍ ፈቃድ ሳቢያ እሰጥ-አገባ ሲገቡ ታዝቤያቸዋለሁ። እናስ ትብብር ማለት ደብዳቤ እስከማድረስ ይሆን እንዴ?....

የስብስቡ "ሰነድ" ራሱን በራሱ ያጋለጠም ይመስለኛል። እንዲህም ይላል– "...የተቃውሞ ጐራ ፓርቲዎች አቅም ውስንነት፣...ለዳያስፖራ አሉታዊ ተፅዕኖ በሩን ክፍት አድርጓል።..." እንደሚታወቀው የተቃውሞው ስብስብ አቅሙን ማሳደግ ያለበት በሀገር ውስጥ እንቅስቃሴው መሆን ይገባዋል።

ዳሩ ግን የኢንጂነር ይልቃልም ይሁን እንደ መድረክና አንድነት ያሉ ፓርቲዎች በራቸውን ለፅንፈኛ ዲያስፖራዎች በርግደው በመክፈት የእነርሱ ተመፅዋች ከሆኑ ሰነባብተዋል። እንዲያውም አንዳንዶቹ አባሎቻቸው ሀገራችን በሽብርተኝነት ከፈረጀቻቸው ቡድኖች ጋር ተመሳጥረው ፓርቲዎቹ ተቋቋሙበት ዓላማ ውጭ ሲንቀሳቀሱ መመልከት የተለመደ ሆኗል። ይህም በፓርቲዎቹ ውስጥ የተሰገሰጉት ግለሰቦች በሰላማዊ ትግል ሽፋን ሽብርተኝነትን ሲያራምዱ እንደነበር የሚያሳይ ነው። ታዲያ እዚህ ላይ የሰማያዊ፣ የአንድነት የአረና አባሎች በዚሁ ተግባር ተጠርጥረው በህግ ጥላ ስር መሆናቸውን መጠቆም ተገቢ ይመስለኛል።

የተቃውሞው ጎራ በሩን ለፅንፈኛ ዲያስፖራዎች ክፍት ማድረጉን ሰሞኑን በአንድነት ፓርቲ ውስጥ የተፈጠረውን ምስቅልቅል በመመልከት ብቻ መገንዘብ ይቻላል። የፓርቲው ሊቀመንበር የነበሩት ኢንጂነር ግዛቸው ሽፈራው በዲያስፖራው ተፅዕኖ ስልጣናቸውን

ማጣታቸውን መናገራቸው ፓርቲውን በውጭ የሚገኘው ፅንፈኛ ዲያስፖራ እንዴት እንደሚያሾረው ሁነኛ አስረጅ ነው።

በአንድ ወቅት ፕሮፌሰር በየነ ጴጥሮስ "ዲያስፖራው ሃምሳ ዶላር እየከፈለ መንግስት እንድንገለብጥለት ይፈልጋል" በማለት የገለፁትንም እዚህ ላይ መጥቀሱ አግባብነት አለው። ከሁሉም በላይ በሀገራችን መንግስት በሽብርተኝነት የተፈረጀው ግንቦት ሰባት የተሰኘው ቡድን ከሻዕቢያ ካገኘው የአምስት መቶ ሺህ ዶላር ውስጥ "አንድ መቶ ሺህ ዶላር ያህሉን ለሀገር ውስጥ ሰላማዊ ትግል መድቤያለሁ" ማለቱ በሰላማዊ መንገድ እንንቀሳቀሳለን የሚሉት የሀገራችን ተቃዋሚዎች በራቸው ለሽብርተኞች፣ ከፍ ሲልም ለኤርትራ መንግስት የብተና ሴራ ምን ያህል ክፍት እንደሆነ የሚያመላክት ነው።

እርግጥ ይህ ዕውነታ 'እንደ ሰማያዊ ዓይነት ፓርቲ ዓይነት ተቃዋሚዎች እፍኝ በማይሞሉ ደጋፊዎቻቸው እየታገዙ ይሆን በፅንፈኛው ዲያስፖራ እየተረዱ በየሳምንቱ ጋዜጣ የሚያሳትሙትና ጠቅላላ ወጪዎቻችን የሚሸፍኑት?፣ ከየትስ በተገኘ ገንዘብ ይሆን ተግባራቸውን የሚከውኑት?' የሚል ጥያቄ ማጫሩ የሚቀር አይመስለኝም። ምላሹ ግን ግልፅ ይመስለኛል–የፋይናንስ ምንጮቻቸው እነማን ሊሆኑ እንደሚችሉ ቀደም ሲል የጠቀስኳቸው ሃቆች አመላካች ናቸውና።

የእንቧይ ብ ስብስቦቹ "ሰነድ" ራሱን የሚያጋልጥ ብቻ ሳይሆን አስቂኝም ጭምር ነው። የሶስት ዓመት ጨቅላ ህፃን ዕድሜን እንኳን ባልደፈነው ሰማያዊ ፓርቲ የሚመራው ስብስቡ "በሰነዱ" ላይ "ኢሕአዴግን ጨምሮ ላለንበት ተጨባጭ ሁኔታ የሚመጥን ዘላቂ መፍትሔ የሚሰጥና የሥርዓት ለውጥ ለማምጣት የሚችል አንድም ፓርቲ የለም፤ ስለሆነም ሁሉን አቀፍ ብሔራዊ መግባባትን መፍጠር ይገባል" ሲል በድፍረት አስፍሯል። እርግጥ ሁሉንም ነገር ለመቃወም የፈለገ ድንጋይን ዳቦ ነው ማለት ይችላል። መብቱም ነው። ግና እርሱ ዳቦ ነው ያለውን ድንጋይ ማወራረድ ያለበት ራሱ ብቻ መሆኑ መዘንጋት የለበትም።

ለመሆኑ "ላለንበት ተጨባጭ ሁኔታ የሚመጥንና ዘላቂ መፍትሔ የሚሰጥ አንድም ፓርቲ የለም" ማለት ከቶ ምን ማለት ይሆን?...በእኔ እምነት ያለንበት ተጨባጭ ሁኔታ ሀገርን በልማት ወደፊት አሳድጎ ሌሎች የደረሱበት የስልጣኔ ደረጃ ላይ መድረስ እንጂ፣ ሰማያዊ ፓርቲና ጭፍሮቹ የሚሹትን በአቋራጭ ስልጣን የማግኘት ቀቢፀ-ተስፋን አይደለም።

ያለንበት ተጨባጭ ሁኔታ ከሀገራችን ጋር የሚስማማ የፖለቲካል ኢኮኖሚ ስሪትን መስርቶ ህዝቡን የሰላም፣ የልማትና የዴሞክራሲ ስርዓት ተጠቃሚ ማድረግ እንጂ ለአክራሪ ኒዮ-ሊበራል ሃይሎች ተላላኪ በመሆን ለቀለም አብዮት ሽር ጉድ ማለት አይደለም። ያለንበት ተጨባጭ ሁኔታ ህግና ስርዓትን አክብሮ፣ የራስን መራጭ ህዝብ ተማምኖ በሰላማዊ መንገድ ለምርጫ መዘጋጀት እንጂ በአጉራ ዘለልነት ህግን እየተፃረሩና "በአክራሪ ኒዮ-ሊበራሎች መጀን" እያሉ የህዝብን ሉዓላዊ የስልጣን ባለቤትነትን መጋፋት አይደለም።

ያም ሆነ ይህ ላለፉት 23 ዓመታት በኢህአዴግ የሚመራው የኢፌዴሪ መንግስት በሀገሪቱ ላይ ታይቶ የማይታወቅ ለውጥ ማምጣቱን እየጎዘዘም ቢሆን መቀበል የግድ ይላል–ዓለም የመሰከረው ዕውነታ ነውና። ፌዴራላዊ ስርዓታችንም ራሱን በራሱ እያረመ ለሀገሪቱ ሁለንተናዊ ለውጥ የበኩሉን ሚና ተጫውቷል። በዚህም ቀደም ሲል የረሃብና የተመፅዋችነት ተምሳሌት የነበረችው ሀገራችን ዛሬ የልማት ተምሳሌት ተደርጋ እየተቆጠረች ነው።

የመላው አፍሪካ ተምሳሌትም ሆናለች። ከተጨባጭ ሁኔታዋ ጋር የሚጣጣም ዴሞክራሲያዊ ስርዓትን መስርታ ባህሉን በመገንባት ላይ ትገኛለች። የስብስቡ ፍጥረትና ትስስርም የዚሁ አባባሌ መገለጫ ነው። ፌዴራላዊ ስርዓቱ በፈጠው ምቹ ሁኔታም የሀገራችን ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ህዝቦች አንድ የፖለቲካና የኢኮኖሚ ማህበረሰብ በመገንባት ብሔራዊ መግባባትን መፍጠር ችለዋል።

ይህም በታላቁ የኢትዮጵያ ህዳሴ ግድብ መገለፁ ይታወቃል። እርግጥም ታላቁ የኢትዮጵያ ህዳሴ ግድብ የህዝቦችን የዘመናት በራስ ሃብት የመልማት ጥያቄን ከከመለስ ባሻገር፣ መላው የሀገሪቱን ህዝብ በቦንድ ግዥ፣ በዕውቀቱና በጉልበቱ ከአራቱም ማዕዘናት ያሰባሰበ ታላቅ ፕሮጀክት ነው።

እናም ለእነ ኢንጂነር ይልቃል ስብስብ ከዚህ በላይ ብሔራዊ መግባባት እንደምን ሊፈጠር እንደሚችል ግልፅ አይደለም። ስብስቡ ለፖለቲካው ፍጆታ ስለሆነ ነው እንጂ ብሔራዊ መግባባት ሁሉን አቀፍ ሊሆን አይችልም። ብሔራዊ መግባባት ማለት ሁሉም የሀገሪቱ ዜጋ በሁሉም ጉዳዮች እንዲስማማ ማድረግ አይደለም። ብሔራዊ መግባባት ተፈጠረ የሚባለው አብዛኛው ዜጋ በተለያዩ ሀገራዊ ጉዳዮች ላይ ተመሳሳይ አቋም ሲይዝ ነው።

እኔ እስሚገባኝ ድረስ ሀገራችን ውስጥ ይህ ሃቅ ዕውን ሆኗል–እንዲያውም ከዚያም በላይ። እናም እነ ኢንጂነር ይልቃል የሚያስቧቸው ፅንፈኞችና አሸባሪዎች አሊያም አክራሪ ኒዮ-ሊበራሎች በተለያዩ ጉዳዩች ላይ ስላልተስማሙ ብሔራዊ መግባባት አልተፈጠረም ማለት አይደለም። ስለሆነም ስብስቡ ብሔራዊ መግባባት እንዴት እንደተፈጠረ ለማየት ከፈለገ ሰሞኑን በቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልል በህዳሴው ግድብ ላይ በሚከበረው ዘጠነኛው የብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ህዝቦች ክብረ በዓል ላይ መመልከት ይችላል።

እዚህ ላይ ግን አንድ ዕውነታን በመጥቀስ ፅሑፌን ልቋጭ። ይኸውም እነ ኢንጂነር ይልቃል እንደሚያስቡት ሀገራችን ውስጥ የስርዓት ለውጥን ማምጣት ቢፈለግ እንኳን፣ ባለቤቶቹ ፓርቲዎች ሳይሆኑ የሀገራችን ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ህዝቦች መሆናቸውን ነው። አንድ ፓርቲ ከአክራሪ ኒዮ-ሊበራል ሃይል ስለታዘዘ ብቻ "የስርዓት ለውጥ" ሊያመጣ አይችልም። መብቱ አይደለም። ወሳኞቹ የሀገራችን ህዝቦች እንጂ ተላላኪው ፓርቲ ሊሆን አይችልም።

ለነገሩ የሀገራችን ህዝቦች ባደረጉት መራር ተጋድሎ የስርዓት ለውጥ ካመጡ 23 ዓመት ሞልቷቸዋል። ከስርዓት ለውጥ ባለፈም የሰላም፣ የልማትና የዴሞክራሲ ጥያቄዎቻቸውን ዕውን ለማድረግ ህገ-መንግስት ቀርፀው በየደረጃው ሁለንተናዊ ተጠቃሚ ከሆኑ 20 ዓመታቸውን ሊደፍኑ የቀራቸው በጣት የሚቆጠሩ ቀናት ብቻ ናቸው። ከዚህ ተጠቃሚነታቸው ሊያናጥባቸው የሚፈልግን ቡድን ዲስኩርን መስማት አይሹም።

ባለፉት አራት ምርጫዎች በዚህ ህገ-መንግስታቸው ላይ የመጡባቸውን ሃይሎች በካርዳቸው እያንኳለሉ እንደቀጧቸው ሁሉ፤ ነገም ቢሆን ይህን መድገማቸው አይቀሬ ነው። እናም ህዝቡ በደሙ የፃፈውን የቃል-ኪዳን ሰነድ መንካት ማለት በራስ ላይ ጥላቻን መጋበዝ ይመስለኛል። ስለሆነም በማወቅም ይሁን ባለማወቅ የእነ ኢንጂነር ይልቃልን መንገድ የተተለሉት የስብስቡ አባላት ቢያንስ ለራሳቸው ሲሉ ህዝቡ እንደ ዓይኑ ብሌን ከሚያየው ህገ-መንግስት ላይ እጃቸውን ማንሳት ያለባቸው ወቅት አሁን ይመስለኛል።